በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኀብረት ውስጥ ያሉ ጥቂት ድርጅቶች እአአ ከጁን 28- ጁን 29 2000 ሺ ዓመት ምህረት ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ስብሰባ አካሂደው መግለጫ ማውጣቸው ታውቋል:: ይህ ስብሰባ ሕገ ወጥ መ ሆኑን በመግለጽ አራት የኀብረቱ አባል ድርጅቶች ከስብሰባው በፊት በጋራ የጻፉትን ደብዳቤና የመላው አማ ራ ሕዝብ ድርጅት ተደረገ ለተባለው ስብሰባ ተወካይ አለመላኩን ለማሳወቅ ያወጣውን መግለጫ ከዚህ ጋር አ ባሪ በማድረግ ሕዝብ እንዲያውቀው አድርገናል ::

መድኅን ፥ ኢብሶ፥ መኢአድ፥ ኢሕአፓ

ሰኔ 20 ቀን 2000 -ዓ.ም.
June 27, 2008

ለ ኢዴኃን ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት
ባሉበት፡-

1. አቶ ፋሲካ በለጠ

2. መቶ አለቃ አያልሰው ደሴ

3. አቶ አረጋዊ በርሄ

4. አምባሰደር በለጠ ረዳ

5. ዶ/ር ሥዩም ገላዬ

6. ዶ/ር ነገደ ጎበዜ

7. አቶ ከፈለኝ አስራት

8. አቶ ኦባንግ ኦኩሙ

9. አቶ ደረጀ ከበደ

ከዚህ በታች ስማችን የተጠቀሰው አራት ድርጅቶች ቀጥለን በምንዘረዝራቸው ምክንያቶች በሰኔ 21 እና 22 2000 ዓ.ም. (ጁን 28 2008 እና በጁን 29 2008) የተወሰኑ የኅብረቱ አባል ድርጅቶች ለማካሄድ ባቀዱት ሕገ ወጥ ስብሰባ ላይ የማንገኝ መሆናችንን እንገልጻለን፡፡

ባለፉት ጥቂት ወራት በኅብረቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያሉ ጥቂት አባላት የኅብረቱን መተዳደሪያ ደንብ የሚጻረር ዴሞክራሲያዊ የአሠራር መርሆዎችን ያፋለሰ  ሂደት ሲከተሉ ቆይተዋል፡፡ ይህ የአሠራር ዝ ፊት አንዲስተካከል ተደጋጋሚ ጥረቶች ቢደረጉም የተወሰኑ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ስህተቶችን በቅንነትና ደንቡን በተከተለ መንገድ  ለማረም ፈቃደኞች ሳይሆኑ ቀርተዋል፡፡ ሕግና ደንብ የተጣሰበት ሁኔታ በግልጽ እየታየ  በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ደረጃ በሕገ ደንቡ መሠረት በቅድሚያ መልስ ማግኘት ያለባቸው ጉዳዮች ሳይጠናቀቁ የሸንጎ ጉባዔ እንዲጠራ ሆኗል፡፡ ስለሆነም የኅብረቱ የመተዳደሪያ ደንብ በሚደነግገው መሠረት እነዚህ ጉዳዮች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ደረጃ እንዲያልቁ አበክረን እንገልጻለን፡፡ ይህሳይፈጸምና የኅብረቱ ሊቀ መንበር የማይከፍተው ጉባዔ ሕገ ወጥ ከመሆኑ ባሻገር ፍሬያማ ሊሆን አይችልም፡፡

የኅብረቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በኢሕአፓ የውስጥ ጉዳይ ያደረገው ጣልቃ ገብነት የኅብረቱን መተዳደሪያ ደንብ የጣሰ ነው፡፡ በኢሕአፓ ውስጥ የነበረውን ችግር ለመፍታት የኅብረቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አንድ ንኡስ ኮሚቴ አቋቁሞ ጉዳዩ በእርቅ እንዲፈታ ያደረገው ጥረት የሚደገፍ ቢሆንም  የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በኢሕአፓ የውስጥ ጉዳይ ላይ መነጋገሩ ተገቢ አልነበረም፡፡ ኢሕአፓ  የኅብረቱ አባል የመሆን መብቱ  ለውይይት መቅረቡ ደንቡን አልተከተለም የሚል ተቃውሞ እየቀረበ በዚህ ጉዳይ ላይ ውይይት ማካሄድና ውሳኔ መወሰን ፍጹም ከሕግ የወጣ በድርጅት ጉዳይ ላይ ጣልቃ የገባ አሠራር ነበር፡፡ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ኢሕአፓ የኅብረቱ አባል ነው፥ በኋላ የተፈጠረው የእነ አቶ መርሻ ቡድን እንደ አዲስ ድርጅት የኅብረቱ አባል ለመሆን ማመልከቻ ካስገባ ሕግና ደንቡ በሚጠይቀው መመዘኛ ተመርምሮ ውሳኔ የሚሰጠው ይሆናል የሚል ስምምነት ላይ ተደርሶ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ስምምነት ተጥሶ ለእነ አቶ መርሻ ቡድን የኅብረት አባል ሆናችኋል የሚል ደብዳቤ እንዲጻፍላቸው ተደርጓል፡፡ ይህ ደብዳቤ የኅብረቱን ውስጠ ደንብ

የሚጻረር ከመሆኑም በላይ ለእነ አቶ መርሻ ቡድንም ትክክል ያልሆነ መልእክት አስተላልፎ ለኅብረቱ ሸንጎና ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተወካዮቻቸውን በደብዳቤ እንዲሰይሙ ምክንያት ሆኗቸዋል፡፡ የኅብረቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስህተቱን በማረም የእነ አቶ መርሻ ቡድን እንደ አዲስ ድርጅት ማመልከቻ እንዲያቀርብ በወሰነው መሠረት ግልጽነት የጎደለውና አሻሚ የሆነ ግን ማመልከቻ እንዲያቀርቡ የሚጠይቅ ደብዳቤ በኅብረቱ ፀሐፊ አማካይነት ተጽፏል፡፡ ኅብረቱ ለጻፈው ደብዳቤ የእነ አቶ መርሻ ቡድን የሰጠው መልስ ኢሕአፓን የምንወክል እኛ ነን የሚልእንጂ ማመልከቻ አልነበረም፡፡ ይህ ደብዳቤ እንደ ማመልከቻ ተቆጥሮ ቡድኑ የኅብረቱ አባል ይሁን አይሁን የሚል ውይይት በሥራ አስጻሚ ኮሚቴ ውስጥ መካሄዱና በዚህ ላይ ተመሥርቶ ውሳኔ ለመድረስ የተደረገው ጥረት አሠራርን የሚጻረር አካሄድ ነበር፡፡

የኅብረቱ ውስጠ ደንብ በሚያዘው መሠረት አንድ አዲስ ድርጅት ማሟላት ያለበት መመዘኛ ሳይመረመርና ሳይረጋገጥ፥ ይህን ቡድን ወደ ኅብረቱ ለማስገባት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ 5 ለ 4 በሆነ ድምፅ የወሰነው ውሳኔ የኅብረቱን ሕገ ደንብ ቁጥር 4.2 በቀጥታ የሚጻረር ነው፡፡ አንድ አዲስ ድርጅት ሲገባ በኅብረቱ ውስጥ ያለውን ድርጅት ቀጥተኛ ስም ያልያዘ መሆን አለበት የሚለውን አንቀጽ በመተላለፍ ከኢሕአፓ ጋር አንድ አይነት ስም፥ አንድ ዓይነት ፕሮግራም፥ አንድ ዓይነት አርማ ያለውን ቡድን ወደ ኅብረቱ ለማስገባት የተደረገው ውሳኔ የኅብረቱን መተዳደሪያ ደንብ የሚጻረር ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዝቅ ብለን እንደምንጠቅሰው ተዋኽድን ያሉ ሁለት ድርጅቶች አንድ ድምፅ ብቻ ሊኖራቸው ሲገባ በነጠላ ሁለት ሆነው ድምፅ መስጠታቸው የኅብረቱን ሕገ ደንብ የሚጥስ እርምጃ ነው፡፡ ሕጉ ይጠበቅ ከተባለ ድምፁ 4 ለ 4 እንጂ 5 ለ4 አልነበረም፡፡ ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ድምፁ 5 ለ 4 የነበረ ቢሆንም አሁንም የኅብረቱ የመተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 4.3 በሚያዘው መሠረት አንድ አዲስ ድርጅት ወደ ኅብረቱ ሊገባ የሚችለው ከተቻለ በሙሉ ስምምነት አለበለዚያ ከጠቅላላው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ቁጥር ውስጥ ሁለት ሶስተኛው ድምፅ ሲሰጡበት ነው፡፡ በሕጉ መሠረት አዲስ ድርጅትን ለመቀበል ከዘጠኝ አባላት መካካል ስድስት አባላት የይሁንታ ድምፅ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ደረጃ የተወሰነው ውድቅ ነበር ማለት ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በኅብረቱ ውስጠ ደንብ መሠረት የአዲስ ድርጅት ጉዳይ ወደ ሸንጎ ሊሄድ የሚችለው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የወሰነውን ውሳኔ ለማጽደቅ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ጉዳይ ወደ ሸንጎ ስብሰባ መተላለፉና እንደ አዲስ እንዲታይ የመነጋገሪያ አጀንዳ መያዙ ሕገ ወጥ ነው፡፡ በስብሰባው ላይ ለመገኘት ያልቻልንበት አንዱ ምክንያት ይህ ጉዳይ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ማለቂያ ሳያገኝ ወደ ሸንጎ እንዲተላለፍ ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ በመወሰኑ ምክንያት ነው፡፡ የኢሕአፓ የውስጥ ጉዳይ ማለቅ ያለበት በኢሕአፓ ብቻ እንጂ በኅብረቱ አይደለም፡፡ አዲስ ድርጅት ከሆነ በኅብረቱ ውስጠ ደንብ መሠረት መመዘኛው ተመርምሮና ተረጋግጦ ወደ ኅብረቱ የማስገባቱ ውሳኔ የአባላቱ ሁለት ሶስተኛ የሆኑት የተስማሙበት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እንጂ ሸንጎ አይደለም፡፡ ሸንጎ ያለው ኃላፊነት የሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴውን ውሳኔ ማጽደቅ ወይም መጣል ብቻ ነው፡

ከላይ እንደገለጽነው ኅብረ ሕዝብና ኢዲዩ ቀደም ብሎ የኅብረቱ አባል ድርጅቶች ቢሆኑም ታህሣሥ 7 ቀን 2000 ዓ.ም. የወጣው መግለጫ ሁለቱ ድርጅቶች " ከታኅሣሥ 5 ቀን 2 ሺ ዓ.ም. ጀምሮ የየግል ኅልውናቸው አክትሞ አንድ ድርጅት በመሆን የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረ ሕዝብ አንድነት ንቅናቄን (ኢዴኃአን) መሥርተዋል" ይላል፡፡ ይህም በይፋ ተነግሯል፡፡ የኅብረት አባል የሚሆኑት የፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ በመሆናቸው በኅብረቱ መተዳደሪያ ደንብ 5.1.1 እና 5.2.1 መሠረት በኅብረቱ ሸንጎ ውስጥም ሆነ በኅብረቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውስጥ ድምፅ መስጠት የሚችሉት የድርጅት ውክልና ያላቸው ብቻ እንጂ በግለሰብ ደረጃ ራሳቸውን የሚወክሉ አይደለም፡፡ ምክትል ሊቀ መንበሩና ፀሐፊው ምንም እንኳ ለዚህ ኃላፊነት በኅብረቱ ሸንጎ የተመረጡ ቢሆንም በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውስጥ የሚሳተፉት ድርጅታቸውን በመወከል እንጂ በግለሰብ ደረጃ አይደለም፡፡ ኅብረ ሕዝብና ኢዲዩ ተዋኽደን አንድ ድርጅት ሆነናል ብለው በይፋ ከገለጹ በኋላ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ውስጥ አባል የሆኑት ምክትል ሊቀ መንበሩና ፀሐፊው በተናጠል ኅብረ

ሕዝብና ኢዲዩን ወክለው ድምፅ ሰጥተዋል፡፡ ኃላፊነታቸውን እስከሚያወርዱ ድረስ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውስጥ ተሳታፊ ቢሆኑም ከተዋኸዱ በኋላ በድምፅ አሰጣጡ ላይ አንደኛው ብቻ ድምፅ መስጠት ነበረበት፡፡ በዚህም የኅብረቱ መተዳደሪያ ደንብ ተጥሷል፡፡ ተጠራ የተባለው የሸንጎ ስብሰባም ላይ ተዋኸደናል ያሉት ድርጅቶች በምን ደረጃ እንደሚሳተፉ ለሥራ አስጻሚው ኮሚቴ የገለጹበት ሁኔታ የለም፡፡ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በዚህ ጉዳይ ላይ ተወያይቶ ግንዛቤ የወሰደበት ሁኔታ የለም፡፡ ይህ ግልጽ ሳይሆን የሸንጎ ስብሰባ መካሄዱ አግባብ ስላልሆነ በተባለው ስብሰባ ላይ ላለመገኘት ወስነናል፡፡

ከላይ በዝርዝር ባስቀመጥናቸው ምክንያቶች አራት ድርጅቶች በስብሰባው ስለማንገኝ ይህ ስብሰባ የሚካሄደው ከስምንት የኅብረቱ አባል ድርጅቶች መካከል በአራቱ ብቻ ይሆናል፡፡ በኅብረቱ የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት ከስምንት ድርጅቶች መካከል አራቱ ብቻ የተገኙበት ስብሰባ ምልተ ጉባዔ የማያሟላ በመሆኑ ስብሰባው ሕገ ወጥ መሆኑን ለማሳወቅ እንወዳለን፡፡ የተጠራው ስብሰባ ሕጋዊ እንዲሆንና ኅብረቱም የተጠናከረ ፀረ ወያኔ እንቅስቃሴውን ማካሄድ እንዲችል የኅብረቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ ደንቡን በተመለከተ ተጠርቶ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ጉድለቶችና ሌሎችም ሕጋዊ እልባት እንዲያገኙ በአንክሮ እያሳሰብን አሁን ሊደረግ የታሰበው ስብሰባ ሕገ ወጥ መሆኑን በድጋሚ እንገልጻለን፡፡

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር

ዶ/ር ሥዩም ገላዬ
የኢትዮጵያ መድሕን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ

አቶ ከፈለኝ አሥራት
የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት

አምባሰደር በለጠ ረዳ
የኦሮሞ ሕዝብ ነፃነት ድርጅት ( ኢብሶ)

አቶ ፋሲካ በለጠ
የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ

ግልባጭ
ለኅብረት ድጋፍ ሰጭ አካሎች
ባሉበት

የመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅት (መዐሕድ)
All Amhara People's Organization (AAPO)

06/30/08

ለሚመለከተው ሁሉ

ውክልና የሌለው ተወካይ

ከመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት

ኢትዮጵያ ሀገራችን በወያኔ ሽፍቶች እጅ ከወደቀችበት ጊዜ ጀምሮ ባለማሰለስ የእነዚህን ዘረኞች የጥፋት አጀንዳ ሲያጋልጥ ቆይቷል።

በተለይም በግንባር ቀደምትነት ተጠቂ ለሆነው ለአማራው ሕዝብ እንዲሁም ወያኔ አራት ኪሎ ሲገባ በአጃቢነት ለታደሙት የጎሳ መሪዎች ነን ባዮች የወያኔን የጥፋት አጀንዳ ከማስፈጸም ያለፈ ቁም ነገር የማይሠሩ መሆኑን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሲገልጽ መቆየቱ የታወቀ ነው።

ከዚህም የተነሳ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ ፍቅርና አክብሮት የነበራቸውን መሪውን ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስን አጥቷል። አሁንም ቢሆን ድርጅቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት ከሚታገሉ ድርጅቶች ጋር ለመሥራት ተቀዳሚ አላማውና መመሪያውም ነው።

በርእሱ እንደተገለጸው በ06/28/08 በአንድ ራዲዮ አቶ ሀይለ ገብርኤል የተባሉ ግለሰብ መላው አማራን ወክለው በአንድ ስብሰባ ላይ ተገኝተዋል ተብሎ ተዘግቧል። ይሁን እንጂ ለተባለው ስብሰባ ድርጅታችን ተወካይ አልላከም። በሕብረቱም ሆነ በመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት ደንብ የውክልና አሰጣጥ መመሪያ አለው። ከዚህ ስርዓትና ደንብ ውጪ ውክልና ሊሰጥም ሆነ ሊኖር አይቻልም። ስለሆነም ስሙ ከላይ የተጠቀሰው ግለሰብ የመላው አማራ ድርጅት ተወካይ አለመሆኑን በትህትና እየገለጽን በተደረገው ግድፈት እጅግ እናዝናለን።

ኢትዮጵያ በልጆቿ ሕብረትና አንድነት ነፃነቷ ተከብሮ ለዘላለም ትኖራለች

የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት